*መስከረም 8ቀን 2002 ዓ.ም*

# *ምርጫና ኮተቱ!*
# *ታዲያ! በኢ.ሕ.አ.ፓ. ላይ ይህ ሁሉ ዘመቻ ለምን ያስፈለጋል...?*

*ከአያልነሽ*

*ጥያቄው አግባብነት ያለውና መሠረታዊ ጥያቄ ነው። በወያኔ አጋፋሪነትና አዝማችነት ከየቦታው ተፈልገው ከጉድጓዳቸው ውስጥ በመውጣት በባነኑ ቁጥር ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉ የደርግ ነፍሰ ገዳዮችና፣ ነፍሳቸውን ደግሞ በወያኔ ቀጭን ገመድ ላይ ያንጠለጠሉ ግለሰቦች ሁሉ ዛሬ "ምርጫ" የሚሉት ቧልት እየተቃረበ ነውና በኢ.ሕ.አ.ፓ ላይ የሰም ማጥፋት ዘመቻና የታሪክ ማውገርገርን ተያይዘውታል። አንዳንዶቹ ደግሞ ዕድሜ ልክ በራሳቸው መቆም ያቃታቸውና ሊቆሙ የተችገሩ የግለሰብ ድርጅቶች በሚያስገርም ሁኔታ የኢ.ሕ.አ.ፓን ሰማዕቶች ስም ሳይቀር በማንሳትና በመጥቀስ ሕይወት እንዳላቸውና "አለንም" ለማለት መሬት ለመሬት ሲሳቡ ይታያሉ። ለሁሉም ግን የምንለው እረ! በሕግ አምላክ! እባካችሁ ሰማዕቶቻችን ይረፉበት! እንላቸዋለን።*

*አንዳንዶች ደግሞ ኢ.ሕ.አ.ፓ "<u>የለም፣ ሞቶም ተቀብሯል</u>" እያሉ 35 ዓመት ሙሉ ላንቃቸው እስኪደርቅ ድረስ ጥሩንባ ሲነፉ እንዳልቆዩ ሁሉ አሁን ደግሞ ከእንቅልፋቸው ባነው፣ ይህንኑ አጥፍተነዋል ያሉትን ደርጅት ኢ.ሕ.አ.ፓን፣ "አርጅቷልና" ከመንገዳችን ገለል ይበል እያሉ ያፏጫሉ። የሚያስቀውና የሚያስደንቀው ደግሞ ኢሕአፓን "አርጅቷል" እና ገለል ይበል የሚሉት ግለሰቦች ሆኑ "ኃይሎች" ያኔ ያኔ ኢሕአፓ ይህንን የገማ አገዛዝ ሲታገል፣ እነርሱ ደግሞ ያንን ታግለን ወደ ትቢያ የቀላቀልነውን የተግማማ ሥርዓት በቀጥታና በእጅ አዙር ያገለግሉ እንደነበር በቂ መረጃዎች አሉ። ታዲያ እነርሱ በሕዝብ ተተፍተው ከነአገዛዛቸው ወደ ትቢያ ተቀላቅለው እያለ፣ እየታገለና በሕዝብ ልብ ውስጥ ያለውን ኢሕአፓ እንዴት አረጀ ብለው ዘበቱበት!...?።*

*አንዳንዶቹ ደግሞ ያወቁ መስሏቸው "**ስለ ኢሕአፓ የምናውቀውን**" በማለት የባጥ የቆጡን ሲዘባርቁም ይደመጣሉ - በአሁኑ ጊዜ ብዙ መናገር አዋቂ አስመስሏልና! ነገር ግን የዚህ ሁሉ መቅበዝበዝና ከወዲያ ወዲህ መራገጥ ዋና ምክንያት አንድና አንድ ብቻ ነው። የኢሕአፓ መኖርና መታገል ከምር የቁም ቅዠት ስለሆነባቸውና ስለሚያባንናቸው ነው። የዛሬን አያድርገውና ትናንትማ፣ የትናንቱ ደርግ/ኢሠፓና የዛሬው መንደርተኛው የወያኔ ተምቾ ኢሕአፓን ከምደረ ገጽ አጥፍተናል ብለውም ነጋሪት ጎሽመው ነበር። ዛሬ ደግሞ ተመልሰው "ጨርሰነዋል" ያሉት ደርጅት ኢሕአፓ በሕይወት አለና እንቅልፍ እየነሳ ከዓይናቸው ብሌን አርቅ ብሎ አስቸግሯልና "አርጅቷል" ማለትን መርጠው ያቅራራሉ፤ ይህን እያሉ መኖር ያፅናናቸዋልና - ጭንቀት የሚወልደው ሰቀቀን!*

*ይህ ብቻ አይደለም። እነኝህ ኃይሎች በዚህ የኢሕአፓ የ37 ዓመት የሞት ሽረት ተጋድሎ በሚያደርግበት ወቅትና ደርግ ሥልጣን ላይ በነበረበትም ጊዜ፣ ስልጣኑን ከያዘው የደርግ አገዛዝ ጋር ተንጠልጥለው (እንዲያውም አንዳንዶቹ መንግስቱ ኃ/ማርያምን እንዲገድል/እንዲጨፈጭፍ ያደርጉት እነሱ ናችው ባዮችም አሉበት) ለዚያ አገዛዝ አጥር ግድግዳው በመሆን ተሰትረው ቆመው ነበር። ነገር ግን አገዛዙን ለመጣል ብርቱ ትግልን ይጠይቅ ነበርና በእርግጠኛነት ደግሞ መውደቅ የነበረበት በመሆኑ ከውድቀት አላዳነም፣ ከውድቀቱም አላዳኑትም፤ ወደ መቃብሩ ሲወርድም በአሳፋሪና በአስገማች ሁኔታ ነበር። ደርግ/ኢሠፓ ለምን ወደ ትቢያ ተቀላቀለ? ወደ ውድቀቱስ ለምን አመራ? ማን ያውራ የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ! ነውና እነሆ!*

*" ለጓድ ሊቀ መንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም*
*ሠላምታ አቀርባለሁኝ! ይላል የሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ደብዳቤ ሲጀምር*

*ጓድ ሊቀመንበር! ከብዙ ሺህ ዓመታት ነፃነት በኋላ ዛሬ ኢትዮጵያ የመጨረሻዋ ደኃ አገር ናት። የዕድገት፣ የሠላም ፖሊሲያችን መሠረት ይህ ሐቅ መሆን አለበት።*

- *ከግማሽ በላይ የአገሪቱ ባጀት ለመከላከያ እየዋለና ፀጥታውም የመሻሻል ሁኔታ በማያሳይበት ወቅት፣*
- *የተለያዩ ተገንጣዮችና ፀረ አብዮት ንቅናቄዎች እየተጠናከሩ በሄዱበት ወቅት፣*
- *ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያዊያን በስደት በዉጭ አገር በሚገኙበት ሁኔታ፣*
- *ረሃብ እየተደጋገመ በመምጣት ከፍተኛ ዕልቂት በሚያስከትልበት ሁኔታ፣*
- *በአገር ውስጥ በሕዝብ መሀከል ያለው ብሶትና ቁጣ እየተስፋፋ በሄደበት ወቅት፣*
- *በኢትዮጵያ ላይ የማያቋርጥ ችግር ለመፍጠር ከሚችሉ መንግሥታት ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሻሻል ብዙ ጥረት በማይደረግበት ሁኔታ..... ኢትዮጵያ ያለችበትን ፍፁም አሳሳቢ ሁኔታ መረዳት አስቸጋሪ አይደለም።*

*ጓድ ሊቀ መንበር! ሁኔታውን መለወጥ ይችላሉ። ይችላሉም ብዬ ስለማመን ነው አለይሉኝታና አለፍርሀት ይህንን ጽሁፍ የማቀርብልዎ....ይላል " የጥቅሱ መጨረሻ....*

*<u>የካቲት 1978ዓ.ም ለመንግስቱ ኃ/ማርያም የተጻፈ ደብዳቤ።</u> ከዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ደብዳቤ ተቀንጭቦ የተወሰደ፣ ሠረዝ የኔ*

*ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ በፀረ ኢትዮጵያዊው ቡድን በወያኔው አገዛዝ ቁም ስቅሏን በምታይበት ሁኔታ፣ አንድ ትውልድ የቀጠፈን የዚያን መታሪ የደርግ/ኢሠፓን አገዛዝ ዝቃጭ ታሪክ ማንሳት፣ "በወደቀ ዛፍ ላይ መረባርብ" ነው ከሚል ኢሕአፓ ብዙ ጊዜ ተቆጥቦ ነበር። መቆጠብ ብቻ ሳይሆን በእርግጠኝነት ከልቡም አምኖበት አደጋ ላይ ለወደቀችው ኢትዮጵያ ቅድሚያ በመስጠትም፣ በየጎሬያቸው ውስጥ ተደብቀው የነበሩና ያን አረመኔ አገዛዝ ሲያገለግሉ የነበሩትን ሁሉ ሳይቀር፣ (እነ ጎሹ ወልዴን ያስታውሷል፣) እጅ ለእጅ እንያያዝና ኢትዮጵያን እናድን/እንታደግ ብሎ ከተደበቁበት በማውጣት አብሮ ጉባዔም ተቀምጦ ነበር። "ከሜጨት መኃል ስለ ፈንግል አይወራም" እንደሚባለው ዛሬ ወያኔ ባለበት፣ ስለወደቀው ዛፍ ስለ ደርግ/ኢሠፓ የጨቀየ ታሪክ መናገር ለወያኔ የልብ ልብ ይሠጣል በሚል በተደጋጋሚያ ከእነኝህ የደርግ ነፍሰ ገዳዮችና ገራፊዎች በየጊዜው ከየአቅጣጫው የሚወረወርበትን ድንጋይና አሉባልታ በትዕግስት ለማሳለፍ መርጦ ነበር። አሁን ግን ከእነርሱ ብሶ ዛሬ ከወያኔ ጋር ተንጠልጥለው በወያኔ አጋፋሪነት ያን እንቁ ትውልድ ትኩር ጥምድ አድርገው ገድሉንም ሊበርዙ ተንስተዋል። "በመስታውት ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው አስቀድሞ ድንጋይ አይወረውርም።" እንላለን*

*ለኢትዮጵያና ለህዝቧ መሠረታዊ ዕድገት ሲል የታገለውን፣ ለዜጎቿ መሠረታዊ መብት ሲል የተዋደቀውን፣ ሉዓላዊነቷ ለተከበረና በዜጎች አንድነት ላይ ለተመሠረተም ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ሲል የደከመውን፣ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ዴሞክራሲያዊ መብት ሲል ቤዛ የሆነውን ያን ትውልድና፤ ከዚያ ትውልድ የተፈጠረውን ኢሕአፓ፣ በወያኔ አዝማችነት የተጋድሎ ታሪኩን፣ ታሪካችንን ጥላሸት ለመቀባት ሲዘሉና ሲፈርጡ ለሚታዩ ኃይሎች "የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ" የሚሉት ዓይነት ነገር ነውና አሁንም ደጋግመን የምንለው "**<u>እየተስተዋለ</u>!**" ነው።*

*የኢሕአፓ ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ነው። ታሪኩም የሚጻፈው በመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ ነው። ሙሉ ታሪኩ የሚገኘውም በኢትዮጵያ ህዝብ እጅ ውስጥ ብቻ ነው፣ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ኢሕአፓ አለ። ታሪክና ንብረትነቱም የኢትዮጵያ ህዝብ እንጅ የአላፊ አገዳሚው መንገደኛ አይደለም። ለምን ቢሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆቹን የገበረበተና የተሳተፈበት ተጋድሎው ነውና!*

## *ወያኔ ለምን በኢሕአፓ ላይ ወቅት እየጠበቀ የስም ማጥፋት ዘመቻ ይከፍታል! ?*

*ወያኔና ኢሕአፓ ይተዋወቃሉ። ትውውቃቸው የወዳጅነት ሳይሆን የባላንጣነት መሆኑ ታሪካቸው ይናገራል። ወያኔና ኢሕአፓ የምርም ባላንጣዎች ናቸው። ባላንጣነታቸው ደግሞ መሠረታዊና ሥር የሰደድ ነው። በኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅሞችና እሴቶች ላይ ደም ያቃባ ፍልሚያም አድርገዋል። **ወያኔ/ህወሓት እና ኢሕአፓ እንደስማቸው የጠለቀ መሠረታዊ ልዩነት አላቸው**። በመሆኑም ወያኔ ከኢሕአፓ ጋር ቀልድ አያውቅም - አይቀልድምም። በእሣት ላይ መጫወት ይሆንበታልና። **ኢሕአፓም** እንዲሁ ከወያኔ ጋር **"መቻቻል"** ብሎ ጨዋታ መጃጃልና መግማማት ባይ ነው - የወያኔን የሆድ ዕቃ ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ጠንቅቆ ያውቀዋልና። እናም የወያኔና የኢሕአፓ ጥል የአንጀት እንጅ በድርድርና በቅልቅል የሚሆን አይደለም። ወያኔም ይህንን ያውቃል። ግን ቢሆንም ዛሬ ለምን በኢሕአፓ ላይ ይሄ ሁሉ ዘመቻ!? ተደጋግሞ መጠየቁ (ጠ ጠበቅ ብላ ትነበብልልኝ) - አቅጣጫን አመላካች ነውና ተገቢ ነው።*

*የ 2002 ዓ.ም ምርጫ የቀረው 280 ቀናት ነው። ወደ 8 ወር አካባቢ መሆኑ ነው። ግን 8 ወር እኮ ብዙ! ነው አይመስላችሁም...? ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! በ6 ወር እንኳ (ያውም እስር ቤት ውስጥ ) 615 ገጽ መጽሐፍ ታትሞ ወጥቷል እንዳትረሱ!....ኡምምምምምምምም !*

*ይህ ምርጫ በራሱ ብዙ ሌላም አስቂኝ ድራማዎች ይዞ ይመጣል። አብሮም ኮተት አለው። በዚህ ሁሉ መሐል ግን ወያኔና ኢሕአፓ ሁሌም እንደተፋጠጡ ናቸው፤ እያልኩ ያለሁት ወያኔና ኢሕአፓ ነው። ወያኔ እና ኢሕአፓ ደግሞ ጠባቸው ዛሬ የጀመረ ሳይሆን 35 ዓመት የቆየ ነው። ለዚህም ነው የተዋወቃሱ የምለው። ከላይ ላስቀምጥ እንደሞከርኩት **ኢሕአፓ እና ወያኔ** በደንብ ይተዋወቃሉ ብያችኋለሁ። በመሆኑም ወያኔ በዚህ ምድር ላይ ከሚፈራውና ከሚያሠጋው ነገር አንዱ የኢሕአፓ መኖር ነው። ወያኔ ዕድሜውን ሲኖር የኖረው፣ ኢሕአፓን እንደሠጋ ነው። ከምርጫው ጋር በተያያዘም የሚሠጋው ኢሕአፓን ነው። ይሄ እውነት ነው፤ ወያኔም ያምናል። ስለሆነም ምርጫ በመጣ ቁጥር ወያኔ ያገለግሉኛል ያላቸውን ከሰማይ በታች ያሉ ማንቸውንም ነገሮች ይጠቀማል- ኢሕአፓን ለመጋተርና ለመከላከል። ኢሕአፓም ይህንን ጠንቅቆ ያውቃል። ኢሕአፓ የሚጨነቀው ወያኔ ተኝቶ ያደረ ቀን ነው የተግባባን መሰለኝ? ለዚህም ነው ወያኔ የደርግ/ኢሠፓ የፀጥታ ሠራተኛ የነበረውን ተስፋዬ እርስቴንም መጽሐፍ አጽፎ የሚያስጮኸው። ይህ ሁሉ ዝም ብሎ በደመ ነፍስ የሚያደርገው አይደለም፤ በደንብ ታስቦና በእቅድ ተይዞ የሚካሄድ ነው።*

*ወያኔ ዛሬ በኢ.ሕ.አ.ፓ ላይ ይሄንን መሳይ መናኛና አልባሌ የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲከፍት የነገሩ አካሄድና አጀማመር ግልፅ፣ እንደ ሰምይ የጠራና እንደ ወርቅም የነጠረ ነው። ወቅቱና ጊዜውም ራሱ በጥንቃቄ ተመርጦና ተረቆ የሚደረግ ነው። ምርጫና እርግጫው! ከምርጫው ጋር በተያያዘ ወደፊት ብዙ እርስቴዎች ጥራዝ፣ ጥራዝ ፅፈው ይዘው ይወጣሉ። ቆርጦ ቀጥሉ ወያኔ ደግሞ የደራረተውን ተረት ያስጮኸዋል። አስታውሱ! ያኔ ወደ መዲናችን እንደገባ ብዙ ሳይቆይ፣ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የመጣበትን የደደቢት ማንፌስቶ ንድፉን **"ተራሮችን ያንቀጠቀጠው ትውልድ"** በሚል አርእስት ሸፍኖ በኢህዴን ጋሻ ጃግሬዎቹ መጽሐፍ አውጥቶ ነበር። አይታክቴ! ገና ወደፊትም ተከታታይ መጽሐፎች ከእስር ቤት ሁሉ ሊሾልኩ ይችላሉ። ልክ እንደ "የነፃነት ጎህ" ዓይነቶች -ምን ችግር አለው! በወያኔ ጊዜ እኮ ጥቁር ወተት ይታለባል የሚባልበት ዘመን ነው።*

*ወያኔ ይህን ሁሉ የስም ማጥፋት ዘመቻ በኢሕአፓ ላይ ማኸጎድጎዱ ታዲያ በስጋት የሚኖር ነውና ለየቀኑ አዳርና ውሎው አፅቅ ያህል ዕድሜ ይሰጠኛል ብሎ ስለሚያስብ ነው። ከዚህ የቧልት*

*ምርጫ ጋር በተያያዘም ብዙ አልባሌና መናኛ የሆኑ የተዛቡ ዜናዎችም (ዲስ-ኢንፎርሜሽን) ይለቃል፣ እናም ኢ.ሕ.አ.ፓን በዚህ መናኛ ቱሉቱላውና ዝባዝንኬ የፈጠራ ወሬው ሊይዘውና ሊጠምደው ይፈልጋል - አዎ! በወያኔ ላይ አልፈርድበትም። ሃሎ! ሃሎ ወያኔ ሆይ! ኢሕአፓም እኮ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ ጉልበቱንና ያለ ኃይሉን በሙሉ የሚያጠፋው በወያኔና ሥርዓቱም እንዲያከትም በማረግ ላይ ነው። በእርግጥ ለወያኔ ኢሕአፓ የጎን ውጋት ነው፣ ሰቅዞ የሚይዘው። ወያኔ የቆመበት መሬት ረግረግ ነው፣ ወያኔ ኢሕአፓ ብብቱ ሥር እንዳለ ያውቀዋል። ስለዚህ ወያኔ የቆመበትና የሚራመድበት መሬት በምላጭ ደንደስ ላይ ስለሆነ ስጋቱ ግልጥ ነው። በግንቦት 7 1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት፣ ወደ ደብረ ዘይት ያስፈረጠጠችው "የቤት ውስጥ አድማ ጥሪ" የመፈለቂያዋ ምንጭ ከየት እንደሆን ወያኔ ጠንቅቆ ያውቃልና ያች ነገር ዳግም እንዳትመለስበት ይቃዣል፣ ይባንናል። ቢሆንም ግን የታምራት ገለታ ጨሌን መቁጠር ብቻውን ለለገሠ ዜናዊ ፍቱን መድኃኒት ሆኖ አልተገኘም።*

*ትዝ ይላችሁ እንደሆን የቅሌት አባት የሆነው ስብሃት ነጋ በ1997 ዓ.ም ግንቦት 20 በምርጫው ማግስት ላይ፣ በወያኔ ፓል ቶክ ላይ ቀርቦ የተናገረውን ዘንግታችሁት ይሆን? ምን አለ መሰላችሁ "**<u>ሕገ-መንግሥታችንን</u> <u>ሊንዱ የቃጡና ያበጡ በውጭ የሚኖሩ ኃይሎችን እብጠት አስትንፍስናል</u>**" እና "**<u>ሬድ ሪቮሊሽን በኦሬንጅ ሪቮልሽን</u>**" ተጠቅልላ ብትመጣም ተርፈናል ብሎ ነበር ሥጋቱን የገለጠው። በውጭ የሚኖሩ? ቅ ቅ ቅ ቅ አይ ፀባይ፤ አጉል ፀባይ! ወያኔ ባላንጣውን በደንብ ያውቃል። ትክክል ነው ማወቁ። አዋቂዎች እንደሚሉትና የፓለቲካ ሳይንሱ ትንታኔም ጠላትና ወዳጅን ያልፈረጅና ያለየ ፖለቲካ ወንዝ አያሻግርም የሚል ፍልስፍናን ያካትታል። በተለይ በተለይ ደግሞ አገርን ለማዳን የሚደረግ ትግል  በእርግጥም ጠላትን አብጠርጥሮና አንጥሮ ማውጣትን ይጠይቃል። ሌላ 3ኛ መንገድ የለም። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጠላት ከትግራይ የፈለሰው የደደቢት ተምቹ ወያኔ ነው፤ አራት ነጥብ። ወያኔና የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ልዩነታቸው መሠረታዊ ነው፤ የትግላቸው ፈረጅም መሠረታዊ ለውጥን የሚጠይቅ ነው። ወያኔ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ እየተፍጨረጨረ ነው፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ አገሩን ከወያኔ ጥፋት ሊጠብቅና ሊያስጠብቅ ተጋድሎ እያደረገ ነው። በዚህ መኃል ሌላ 3ኛ የሰርጥ መንገድ የለም።* **ድርድር፣ ቅልቅል፣ መቻቻል፣ "ምሕዳር ማስፋት"፣ "ምሕዳር ማጥበብ" አስመራጭ ቦርድ፣ አገናኝ ቦርድ፣ ፔትሽን አስፈራሚ፣ ድንበር ኮሚሽን ቦርድ፣ ከዳኮታ ኤ.ኤ.ፍ.ዲ.፣ ከለንደን ሠራዊት፣ ከምፅዋ ኢትዮጵያዊነት፣ ገለመሌ** *የሚባሉ ትግል ማዘናጊያዎች በሙሉ ቦታ የላቸውምና ኅበዝ እንቃ !*

*በዚህ አጋጣሚ ደግሞ አንዲት ነገር ታሰበችኝ፥ ማለም አይከለከል። "የቡርቃ ዝምታ" መጽሐፍ ባለቤት የሆነው የ"ጋዜጠኛው ማስታወሻን" 2ኛ ክፍል ምርጫ 2002 ከመድረሱ በፊት 3 ወር ሲቀረው ይዤ እቀርባለሁ ያለ መሰለኝ፣. ደግ ያድረሰን። ከዚያ በኋላ ደግሞ እባክህን* **"ከእሣት ወደ ረመጥ"** *በሚል አርእስት ሥር ስለ አደዬ - ባህረ ነጋሽ ልትጽፍልን ብትሞክር! እሺ.....?*

***<u>ማሳሰቢያ!</u>***

*የዓይንሽ ቀለም አላማረንም ብላችሁ የምተኩሱ ካላችሁ ዕድሜ ለ"ኅረቤት አሥመሪና" አስጠጊኝ ብዬ ከለላ እለምናለሁ - ጨረስኩ።* **ኡፕስስስስስስስስስስ......***ማዕሌሽ ወዲ አፈወርቂ!*

*የሕዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!*
*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!*
*መልካም አዲስ ዓመት ለኢትዮጵያዊያን!*
*ቸር ይግጠመን!*
*september_2009*